**የአ/ል/ወ/አቅ/ግ/ጽ/ቤት**

1. **ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ**

   ከሐምሌ 2001 - ሰኔ 30/2001 ዓ/ም

2. **ቁልፍ የትኩረት መስኮች**

የታቀዱ ቁልፍ የትኩረት መስኮች

3.1.1. 100% በሰው ሀይል ተሟልተው ሙሉ ትግ በራ የጀመሩ 7 ጽ/ቤቶች

3.1.2. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በጀመሩ 7 ጽ/ቤቶችና የተፈሠረ አሠራር፣ የተደረገ ድጋፍና ክትትል

3.1.3. በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ሥርዓት ላይ የሰለጠኑ የ7 ጽ/ቤቶ 180 ሠራተኞችና 38 የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች

3.1.4. በ7 ጽ/ቤቶች የተደረገ የሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ አተገባበር ድጋፋዊ ክትትል የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ ለሙከራና ለሙሉ ትግበራ ዝግጅት ላይ ላሉ 10 ጽ/ቤቶች የተሰጠ ድጋፍ

3.1.5. በለውጥና ለመሪነት በተመረጡ ርዕሶች ላይ ተከታታይነት ያለውን ሥልጠና የወሰዱ 68 የጽ/ቤት ኃላፊዎችና የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች

3.1.6. የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞቻችን 10 ተግባራዊና ውጤታማ እንዲሆኑ ለ17 ጽ/ቤቶች የተፈጠሩ አሠራሮች

3.1.7. ስምንቱ የመልካም አስ/ፓኬጆች ውጤታማና የማስፈጸም አቅም እንዲሆኑ በ33 ቀበሌ የተዘረጋ አሠራር

3.1.8. ሕ/ሰቡ 100ኽ የመልካም አስ/ተጠቃሚ እንዲሆን በ33 ቀበሌ የተጠናከረ የሥራ አስኪያጆች አሠራር

3.1.9. ተባዝተውና ተጠርዘው ለ17/ጽ/ቤቶችና ለ33 ቀበሌያት የተሠራጩ መመሪያዎች ፣ደንበኞች፣አዋጆችና የሥልጠና ማኑዋሎች

3.1.10. የማስፈጸም አቅማቸው የተገነባ 17 ጽ/ቤቶች ሠራተኞችና የ33 ቀበሌ አመራር አካላት

3.1.11. ከሰባቱ የጽ/ቤት ኃላፊዎችና ከየሥራ ሂደቱ አስተባባሪዎች ጋር የተደረገና የተፈፀመ የአፈጻጸም ውል ስምምነት

4. **የተፈፀሙ ዝርዝር ቁልፍ የትኩረት መስኮች**

4.1. 85% በሰው ሃይል ተሟልተው ሙሉ ትግብራ የጀመሩ 7 ጽ/ቤቶች

- ምደባው በደንብ 72/2001 መሠረት እንዲፈጸም የተደረገ ድጋፍና ክትትል

- የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና የወሰዱ 400 ሠራተኞች
- ለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሥልጠና ከክልል አቅ/ግ/ቢሮ የተመደበ 130000 ብር እና በትርፍነት ከክልል ፋ/ቢሮ የተመለሰ ብር 20600

4.2. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በጀመሩ 7 ጽ/ቤቶች የተፈጠረ አሠራርና የተደረገ ድጋፍና ክትትል

- ከክልል የተላከና የተሠራጨ ቼክ ሊስት
- በቼክ ሊስቱ መሠረት በስትሪንግ ኮሚቴ የተገመገመ አፈጻጸም ምቹ ሁኔታ የተፈጠረላቸው ሥራ ሂደቶች
- በወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ የተገመገመ የብፐርትግበራ
- የሰው ሃይልና የበጀት ዕጥረት ችግራቸው እንዲፈታ ለወረዳ አስ/ጥያቄ የቀረበላቸው 7 ጽ/ቤቶች

4.3. የአቅም ግንባታ ፕሮግራች 100 ተግባራዊና ውጤታማ እንዲሆኑ በ17 ጽ/ቤቶች የተፈጠሩ  አሠራሮች

- በየሥራ ሂደቱ በተቀመጡ ስታንዳርዶችና ፎርማቶች መሠረት ሥራዎች እንዲሠሩ የተደረገ ድጋፍና ክትትል
- የአገልግሎት አሰጣጥን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ ተዘጋጅተው ለ17 ጽ/ቤቶች የተሠራጨ 5 ዓይነት ቅጻቅጽ
- ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ምቹ ሆነው የተዘጋጀና የተሰራጨ የክስና የዋስትና ማመልከቻ ቅፆች
- ለክትትልና ለድጋፍ ምቹ ሆነው የተዘጋጁና የተሰራጩ 5 ዓይነት ቼክ ሊስቶች
- በወር 2 ጊዜ ለሁለት ስዓት ክትትልና ድጋፍ የሚያደርጉና ክፍተትን  በመሙላት ግብረ መልስ የሰጡ የጽ/ቤታችን ባለሙያዎች
- ጽ/ቤቶች ለተገልጋይ ምቹ እንዲሆኑና የለውጥ ቦታና ምልክቶች እንዲታዩ በግርግዳ፣በታፔላና በማስታወቂያ ቦርድ እየተሠሩ ያሉ አነቃቂ ሥራዎች

4.4. ስምንቱ የመልካም አስተዳደር ፓኬጆች ውጤታማና የማስፈጸም አቅም

- እንዲሆኑ በ33 ቀበሌያት የተዘረጋ አሠራር

- በስምንቱ ፓኬጆች የሚሠሩ ሥራዎችን የሚገልጽ የተሠራጨ ማንዋል
- በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ላይ ሥልጠና የወሰዱ 24 የጽ/ቤት ኃላፊዎችና 33 የቀበሌ አስተዳደሮችና ሥራ አሰኪያጆች
- ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲረዱ የተዘጋጁና የተሠራጩ 5 ቅጻቅፆች
- ለድጋፍና ለክትትል ምቹ ሆነው የተዘጋጁና የተሠራጨ 1 ቼክ ሊስት
- በ3 ወር 1 ጊዜ ለ2 ስዓት በ33 ቀበሌያት ክትትልና ድጋፍ ያደረጉ 2 የጽ/ቤት ባለሙያዎች
- የአፈጻጸም ውል ስምምነት ከጽ/ቤታችን ጋር የፈጸሙ የ33 ቀበሌ አስተዳዳሪዎችና ሥራ አስኪያጆች

4.5. የማስፈጸም አቅማቸው የተገነባ የ17 ጽ/ቤት ሠራተኞችና የ33 ቀበሌ አመራር አካላት

- በተመረጡ 7 ርዕሶች ላይ ሥልጠና የወሰዱ 33 ሥራ አስኪያጆች
- በመልካም አስተዳደር ፓኬጆች ላይ ሥልጠና የወሰዱ 24 የጽ/ቤት ኃላፊዎችና 33የቀበሌ አስተዳደሮች
- በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ከቡርጂ፣ከአማሮ፣ከጌዲኦ ለተውጣጡ በ5 ቀናት በሰው ሀብት አመራር ባለሙያዎች የተሰጠ ሥልጠና
- ለልዩ ወረዳው 10 የግብረ ሀይል አባላት የተሠጠ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና
- ለ45 ቀናት ከየጽ/ቤቱ ለተውጣጡ 16 ሠራተኞች በኮምፒዩተር መሠረታዊ እውቀት የተሰጠ ሥልጠና
- በ ፅብአ መሥመር አጠቃቀም አገልግሎት እንዲሰጥ የተደረገ የፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት
- ጥገና የተደረገላቸው ሁለት ኮምፒዩተርና 1 ፎቶ ኮፒ ማሽን
- 8 ሠራተኞች ለመጀመሪያ ዲግሪ 3 ሠራተኞች ለ2ኛ ዲግሪ የተላኩ ሠራተኞች
- ለአቅም ግንባታ ሥልጠና በጀት ለማፈላለግ ተዘጋጅቶ የተሠራጨ 1 ፕሮጀክት ፕሮፖዛል

- የሥራ ስፋት ላለባቸው ጽ/ቤቶች የተሠራጨ ሁለት እስካነሮችና አንድ ኮምፒዩተር
- በልዩ ወረዳው ም/ቤት ለ26 ቋሚ ኮሚቴዎችና ለ66 አፈ ጉባኤዎች የተሰጠ ሥልጠና
- በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የሰለጠኑ 136 የግብርና ባለሙያዎችና 36 የፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ባለሙያዎች
- ሕ/ሰቡ 100% የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ እንዲሆን በ33 ቀበሌ የተጠናከረ የሥራ አስኪያጆች አሠራር

4.6. በ33 ቀበሌ የተጠናከረ የሥራ አስኪያጆች አሠራር

- በ33 ቀበሌ በቀን ለ8 ሰዓት አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጀና የተደራጀ ጽ/ቤት
- በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በቂ ግንዛቤ የጨበጡና የተለወጡ 33 ሥራ አስኪያጆች
- በሥራ አስኪያጆች ተከታታይነት ያለውን ድጋፍ የሚሰጡና የተመደቡ 2 የጽ/ቤታችን ባለሙያዎች
- የአፈጻጸም ውል ስምምነት የፈረሙና በውጤት ተኮር ዕቅድ የሚመሩ 33 ሥራ አስኪያጆች
- በ6ወር 2 ጊዜ ድጋፍና ክትትል የተደረገላቸው የ33 ቀበሌያት ሥራ አስኪያጆች

4.7.ተባዝተውና ተጠርዘው ለ17 ጽ/ቤቶችና ለ33 ቀበሌያት የተሠራጩ መመሪያዎች፣ ደንቦችና አዋጆች

- ከክልል የተላለፈና ለ33 ቀበሌያት የተሠራጩ የመልካም አስተዳደር ፓኬጆችና የሥራ አስኪያጆች አሠራር መመሪያ
- የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራን ማስፈጸሚያ ደንብ ለ17 ጽ/ቤቶች የተሠራጨ
- ከክልል የሚመጡ የተለያዩ መመሪያዎችና ማሻሻያ ደብዳቤዎች ለ17 ጽ/ቤቶች የተሠራጩ
- ከክልል የመጣና ለ17 ጽ/ቤት የተሠራጨ የዲስፕሊን መመሪያ

- ለ33 ቀበሌያት የተሠራጨ የሥልጠና ማኑዋሎች

2. ያልተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት

5.1. በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ሥርዓት ላይ የሰለጠነ የ7 ጽ/ቤቶች 180 ሠራተኞችና 38  የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች

5.2. በ7 ጽ/ቤቶች የተደረገ የውጤት ተኮር ዕቅድ አተገባበር ድጋፋዊ ክትትል

5.3. ከ7ቱ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ከሥራ ሂደት አስተባባሪዎች ጋር የተደረገ የአፈጻጸም ውል ስምምነት

6. <u>ዓበይት የትኩረት መስክ</u>

6.1. <u>የታቀዱ ዐበይት የትኩረት መስኮች</u>

6.1.1. ሁሉም ዜጎች እኩል መብታቸው ተጠብቆ ሊዳኙ እንዲችሉና ፍትሃዊና ትክክለኛ ሥራ እንዲሠራ የተፈጠረ አሰራር

6.1.2. የኬሌ ከተማና በገጠር ቀበሌዎች የቀነሱ ወንጀሎችና የወንጀለኛ ቁጥር

6.1.3. የተቀመጠላቸውን ተደራሽ ግቦችና ስታንዳርድ ለማሳካት በዕቅድ የሚመሩ፣ ፕሮግራማቸውንና አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማሳወቅ እየሠሩ ያሉ የጽ/ቤታችን

4

ዋናና 2 ድጋፊ የሥራ ሂደቶች

6.1.4. በ33ቱም ቀበሌያት በመልካም አስተዳደርና በልማቱ ሞዴሎች እንዲፈጠሩ እየተሠራ ያለ ተከታታይነት ያለው ሥራ

6.1.5. ለተንሳፋፊና በተለያዩ ምክንያት ምደባ ባልተሰጣቸው ሠራተኞች ምደባ እንዲያኙ የመፍትሄ አማራጭበመፈለግ 100% የተከናወነ ተግበር

6.1.6. የሽቦ አልባ ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ 33 ቀበሌያት

6.1.7. በጀነሬተር በሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ 7 ጽ/ቤቶች

6.1.8. ከአርሶአደር አርሶአደር፣ከልማት ቡድን ወደ ልማት ቡድን ከቀበሌ ወደ ቀበሌ ፣ ከወረዳ ወደ ክልል ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲንሳፋፉ የተዘረጋ አሠራር

6.1.9. በታቀደላቸው ጊዜ ገደብ መሠረት ለሚመለከተው አካል የቀረቡ ተአማኒነት ያላቸው ሪፖርቶች

6.1.10. ከ17 ጽ/ቤቶች ጋር የተፈጠረ ጤናማና ጠንካራ ግንኙነት

6.2. <u>የተፈፀሙ ዝርዝር ዓበይት ተግባራት</u>

6.2.1. ሁሉም ዜጎች እኩል መብታቸው ተጠብቆ ሊዳኙ እንዲችሉ ፍትሃዊና ትክክለኛ ሥራ እንዲሠራ የተዘጋጀ አሠራር

- በተዘዋዋሪ ችሎት አፋጣኝ ውሳኔን በመስጠት የተጀመረና 2 ዙር የተሰየመ ችሎት
- ለተዘዋዋሪ ችሎት የተመደበና የተፈጸመ በጀት 3600 ብር
- ከተለያዩ ጽ/ቤት ከተገልጋዮች የቀረበውን ቅሬታ በማጣራትና አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የተፈቱ ችግሮች
- ለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ትግበራ የሰው ኃይል ድልድል አፈጻጸም በደንቡ መሠረት መመደቡ የተገመገመና እንዲስተካከሉ የተደረጉ ምደባዎች
- በፍትሃዊ አሠራር ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ 11 የመንግስት ሠራተኞች
- በ33ቱ ቀበሌያት ያሉና የተጠናከሩ የማህበራዊ ፍ/ሸንጎ አሠራሮች

6.2.2. በኬሌ ከተማና በገጠር ቀበሌዎች የቀነሱ ወንጀሎችና የወንጀለኛ ቁጥር

- በ33ቱም ቀበሌያት የተመደቡ የወንጀል መከላከል ፖሊስ ኃይል
-
-
- በ33ቱም ቀበሌያት የተፈጠሩ ህ/ሰብ አቀፍ ወንጀል መከላከል ኃይል ወይም ኮሚኒቲ ፖሊሲንግ
- አብዛኛውን ጊዜ በልማት ላይ እንዲያሳልፍ የተደረገ ህ/ሰብ
- በፖሊስ ጣቢያ የቀነሱ የእስረኞች ቁጥር

6.2.3. የተቀመጠላቸውን ተደራሽ ግቦችና ስታንዳርድ ለማሳካት በዕቅድ የሚመሩ፣ ፕሮግራማቸውን አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማሳወቅ እየተሠሩ ያሉ የጽ/ቤታችን 4 ዋናና 2 ደጋፊ የሥራ ሂደቶች

- የአገልግሎት ዝርዝርን፣ ዓላማንና የተለያዩ መረጃዎችን የሚገልጹ የተዘጋጁና በተገልጋዮች የተሠራጩ ብሩሽሮች
- በአራት ዋና በሁለት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች የታቀደ አንድ የ2002 የፋይናንስ ፍላጎት ዕቅድ
- ተከልሶ የታቀደ የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት የ2001/2002 ዓ/ም ዕቅድ
- በህፅቫሐጽዕድስ በሥርዓት ጾታ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተሠራጩ በራሪ ጽሁፎች፣ ብሮሽሮች፣ ኮንደሞችና የተደረገ ውይይት
- ፈጣን የሥልጠናና የትምህርት መጋበዣያ ማስታወቂያዎች
- በቢሮ ፣በወንበርና ጠረንጴዛ ተደራጅተው ሥራ የጀመሩ 4 ዋናና 2 ድጋፍ የሥራ ሂደቶች

6.2.4. በ33ቱም ቀበሌያት በመልካም አስተዳደር በልማቱ ሞዴሎች እንፈጠሩ እየተሠራ ያለ ተከታታይነት ያለው ሥራ

- ለ900 የልማት ቡድን መሪዎችና ለኮሚቴዎች የለውጥ ተነሳሽነትን ለመፍጠር በ33ቱም ቀበሌ ለ1 ዙር የተደረገ ድጋፍና ምክክር
- ለቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ለ1 ዙር የተደረገ ድጋፍና ክትትል

ለተንሳፋፊና በተለያዩ ምክንያት ምደባ ላልተሠጣቸው ሠራተኞች ምደባ እንዲያገኙ የመፍትሄ አማራጭ በመፈለግ 100ሺ የተከናወነ ተግባር

- ተንሳፋፊ ሆነው በግብረ ሃይል ምደባ ያገኙ 7 ሠራተኞች ፣ 6 በትምህርት፣ 38 በማቋቋሚያ፣ 6 በጡረታ በግብረ ኃይል አማራጭ የተፈለገላቸው ሠራተኞች
- ከሹመት ወርደው ምደባ የተሰጣቸው 6 ሠራተኞች
- ትምህርት ላይ ቆይተው ምደባ ያገኙ 2 ሠራተኞች

6.2.6 ሽቦ አልባ ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ለሆኑ 33 ቀበሌያት የተደረገ ድጋፍ

- ሲበላሹ እንዲጠገኑ የተደረጉ የ10 ቀበሌ ስልኮች

6.2.7 በጀነሬተር በሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረጉ 5 ጽ/ቤቶች

- ተጠግኖ ሥራ እንዲጀምር የተደረገ 1 ጀነሬተር
- በ300 ሜትር ርቀት የኤሌክትሪክ መሥመር የተዘጋጀላቸው 5 ጽ/ቤቶች
-
-
- ለጀነሬተር ጥገና፣ ለመስመር ዝርጋታና ለነዳጅ ከዋና አስ/ጽ/ቤት የተመደበ ብር 8000

- ዋናው ኤሌክትሪክ በሌለበት ወቅት ከጀነሬተር  በሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ የሆኑ 7 ጽ/ቤት

- 6.2.9. በታቀዱላቸው ጊዜ ገደብ መሠረት ለሚመለከታቸው አካል የቀረቡ 100%
- ተአማኒነት ያላቸው ሪፖርቶችና መረጃዎች
- ለወረዳው ም/ቤትና ለክልል አቅ/ግ/በሮ ተዘጋጅቶ የቀረበ የ6 ወር ሪፖርትና የ12 ወር ሪፖርት
- የተሰበሰበና የተደራጀ የመ/ቤቱ 13 ሠራተኞች መረጃ
- ለክልል አቅ/ግ/ቢሮ ሪፖርት የተደረገ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ አፈጻጸምና የሰው ኃይል መረጃ
- ከ17 ጽ/ቤቶች ጋር የተፈጠረ ጠንካራና ጤናማ ግንኙነት
- ከቁጥጥርና ግምገማ ነጻ የሆነ የተፈጠረ ድጋፍና ክትትል

ከጽ/ቤቶች የቀረቡ ጥያቄዎች መሠረት የተሰጠ የማማከርና መረጃ የመስጠት አገልግሎት

6.3. <u>ያልተፈጸሙ ዝርዝር ዓበይት ተግባራት</u>

6.3.1. በክስና በማመልከቻ አቀራረብ ሥርዓት የተጀመረ ፈጣን አገልግሎት

6.3.2. በጽሁፍ፣ በምስልና በድምጽ የተቀረፁና የተቀመሩ የምርጥ ተሞክሮዎች መረጃዎች

6.3.3. በ33ቱም ቀበሌያት የተስፋፋና ያደገ ምርጥ ተሞክሮ

6.3.4. ተዘጋጅቶ ለክልል አቅ/ግ/ቢሮ በወቅቱ ያልቀረበ የ9 ወር የ2001 ዓ/ም የክንውን ሪፖርት

6.3.5. አስተያየትና ግብረ መልስ የማሳሰብና ለአፈጻጸም ሂደት ተገምግሞ የተዘጋጀ ግብዓት

6.3.6. ከአርሶአደር አርሶአደር፣ ከልማት ቡድን ወደ ልማት ቡድን፣ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ ፣ ከወረዳ ወደ ክልል ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ የተዘረጋ አሠራር

7. <u>የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ በመቶ</u>

7.1. በቁልፍ ተግባር     66%

7.2. በዓበይት »     70%

8. <u>በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች</u>

8.1. ጠንካራ ጎኖች

በክልል አቅም ግንባታ ቢሮ የተሰጠው የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለዕቅድ አፈጻጸም አቅም መፍጠር

- በአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ያሉ ባለሙያዎችና የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ለለውጥ ያላቸው ተነሳሽነትና ዝግጅት
- ዋና አስ/ጽ/ቤት ለሥራ አስኪያጆች ሥልጠና የሚሆን በጀት ብር 14000 መመደቡ
- በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ውስጥ የገቡ ጽ/ቤቶች አስተባባሪዎችና ፈጻሚዎች ያላቸው የአመለካከት ለውጥ
- ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ የሆኑ ቅጻቅፆችና ቼክ ሊስቶችን በየዕለት ሥራንና ለውጥን መመዝገቢያ ቅፆች ዳብረውና ተሻሽለው መዘጋጀታቸው
- የሥራ ሂደቶች በራሳቸው ፈጽመውና ወስነው መሥራታቸው
- ለሥራ አስኪያጆችና ለቀበሌ አስተዳዳሪዎች የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥልጠና መሰጠቱ
- የጽ/ቤታችን ባለሙያዎች በተመደቡባቸው ቀበሌያትና ጽ/ቤት ተገኝተው ከ4ሰዓት እስከ 1 ቀን ተተክለው መደገፋቸው
- መሠረታዊ የኮምፒዩተር ሥልጠና 10 መንግስት ሠራተኞች መሠጠቱ
- የመብራት አገልግሎት ለ5 ጽ/ቤቶች እንዲዳረስ መደረጉ
- ለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ለተደለደቡ ሠራተኞች ሥልጠና ከክልል አቅ/ግ/ቢሮ በጀት መመደቡ

### 8.2.ደካማ ጎኖች

- በተለያዩ ደራሽ ሥራዎች በመወጠር ዕቅድን 100 አለማሳካትና የ9 ወር ሪፖርትንም ለክልል አቅ/ግ/ቢሮ በወቅቱ አለመላክ
- አንዳንድ ጽ/ቤቶች የተጠየቁትን መረጃም ሆነ የአፈጻጸም ሪፖርት በተጠየቁበት ጊዜ ያለማቅረብና የ/ብፐርሐ አፈጻጸምን በስትሪንግ ኮሚቴ ያለመገምገም
- የሚዛናዊ ውጤት ተኮር /ብስችሐ አፈጻጸም መዘግየት
- የተመደበ የሰው ኃይል እጥረት በተለይ በለውጥ ፕ/ፕ/ትግበራ ሥራ ሂደት
- ለየሥራ ሂደቶች ኮምፒዩተር አለመኖርና የበጀት ዕጥረት መኖር
- የተሽከርካሪ በተለይ የሞተር ሳይክል አለመኖር በክትትልና ድጋፍ ችግር መፍጠሩ
- የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ አለመሆን
- የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ሥልጠናን ያልወሰዱ ባለሙያዎች መኖር
- የቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ያለመጀመር
- የበጀት ዕጥረት መኖር

### 9. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ከዕቅድ ክንውን ጊዜ ውጪ ቢሆንም ለማከናወን ጥረት መደረጉ
- ባለው የሰው ኃይል ጫና ፈጥሮ ዕቅድን ማከናወን

- ❖ በጽ/ቤቱ ባለው አንድ ኮምፒዩተር ተጨናንቆ የመጠቀም
- ❖ ተሽከርካሪ በመዋስና በእግር በመመላለስ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- ❖ ሥልጠና ላልወሰዱ ለጽ/ቤታችን ባለሙያዎች ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ

## 1. ወደፊት ትኩረት የሚወሰድባቸው ጉዳዮች

10.1. በቂ በጀት መመደብ

10.2.ተሽከርካሪ በተለይ ሞተርሣይክል ማስመደብ

10.3. በጥናቱ ላይ የተቀመጠው የሰው ኃይል ያነሰ በመሆኑ እንዲጨመር በተለይ በለውጥ ፕ/ፕ/ት/ዋና ሥራ ሂደት

10.4. መንግስታዊ የሆኑና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባጠቃላይ ለማስፈጸም አቅም ልዩ ትኩረት በመስጠት መረባረብ

10.5. ተከታታይነት ያለውን ሥልጠና ለባለሙያዎች ያለመሰልቸት መስጠት

10.6. የሚዛናዊ የውጤት ተኮር አፈጻጸም ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ

10.7.ከዕቅድ ውጪ በሆኑ ተደራሽ ሥራዎች አመራሩ እንዳይወጠር ማድረግ

10.8.በኮምፒዩተር ሥራ ሂደቶችን ማደራጀትና እርስ በእርስ በማገናኘት የኢንተርኔት ተጠቃሚ ማድረግ

**ማሳሰቢያ** ከ1-8 የተገለፁት መፍትሄ ቢያገኙና በአዲሱ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በተቀመጡ ተደራሽ ግቦችን መሠረት ሁሉም ትኩረት ሰጥቶ ኃላፊነቱን ቢወጣ የአቅም ግንባታ ራዕይ በአጭር ጊዜ ይሳካል።